# "**<u>ውሸትና ስንቅ እያደረ ይቀላል</u>**"!!!

ከባህልቢ ዘማርያም

**<u>ክፍል ስድስት</u>**

አንባቢዎቹን ስለ መስቀል ትውስታዎቼ ለማጋራት ሓሳብ የነበረኝ ቢሆንም፤ ጊዜ አላዳርስ ብሎኛልና እስክመለስበት ድረስ እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሰላም አደረሰን እያልኩ ክፍል ስድስት መጣጥፌን ቀጥሎ አቀርባለሁ። በዚህ ክፍል መጨረሻ ላይ በሐጎስ ዮሐንስ ጽሑፉ ቅደም ተከተል መሠረት ሰፍሮ የሚገኘው ስለ ቅዠታቸው ያሰፈሩት ነገር ይበልጥ የሚያስተዛዝብ ሆኖ ይገኛል። ለማነኛውም እናንተ አንባቢዎቼ እንድትፈርዱት የምለው አለኝና ተከታተሉኝ።

(የሐጎሰ ዮሐንስ ፅሑፍ ፓራግራፍ 6 11ኛ መስመርን ይመልከቱ)

> ***"…. ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ በሽሙጥና በውስጠ ታዋቂያዊ አነጋገር ምናልባት በአሜሪካና ኤውሮጳ በሚኖሩት ላይ ያነጣጠረ በሚመስል መልኩ ይገልፁታል።"***

በዚህ መስመር ውስጥ "አመልካች የሚመስል" (….may refer to …) የሚል አባባል ተጠቅሶ ይገኛል። እዚህ ላይ ልጆቻቸው ወደ ኤርትራ የኮበለሉባቸው ቤተ-ሰቦች በአሜሪካና በኤውሮጳ የሚኖሩ የኢሮብ ተወላጆች ልጆቻችንን ወደ ኤርትራ እያስኮበለሏቸው ነው ብለው ነግረውኛል የሚሉትን ያላቸው ስለሌለና ማን አለህ የሚል ጥያቄን ስለሚያስከትል መድፈር አልቻሉም። ስለሆነም፤ ሐጎስ የተጠናወታቸው ወሬን የመፍጠር አባዜ ችላ ላለማለት የራሳቸውን እድምታ በመጨመር ልጆቻቸው የኮበለሉባቸው ወላጆች ነገሩኝ የሚሉትን የራሳቸው ትርጉም በመሥጠት "አሜሪካና ኤውሮጳ የሚኖሩትን" እንደሚያመላክት በሚያስመስል መልኩ የራሳቸውን ስንጥር አካትተውበታል። ይህ ደግሞ በምን ምክንያት እንደሆነ ግልጽ ባይሆንም፤ ሐጎስ ዮሐንስ በፈጠራ ወሬ ሊያሸብሯቸው የሚፈልጉዋቸውና ለማሸበሩ ዓላማ ተደርገው የተቀመጡ ሰዎች እንዳሉ ያመላክታል። ባይሆን ኖሮ ሐጎስ ዮሐንስ ይህን ዓይነት ከባድ ውንጀላ ይዘው ሲቀርቡ ሐላፊነት የሚሰማው ሰው ማድረግ እንደሚጠበቅበት ወንጀሉን የማጣራት ሥራ መሥራት እንኳ ባይችሉ፤ አሉባልታውን ራሳቸው ከሚፈጥሩት፤ እነዛ ነገሩኝ የሚሏቸው ቤተ-ሰቦች (እንደሌሉ ይህ ፀሐፊ ከልብ ቢያምንም ለሐጎስ ዮሐንስ ይመቻቸው ዘንድ ዕድሉን ላለመንፈግ) ማንን እንደሚጠረጥሩ በመጠየቅ ሃቁን ከነሱ ለማግኘት ቢሞክሩና ያንን እንዳለ ቢያሰፍሩ የተሻለ በሆነ ነበር። ሆኖም፤ ለተወሰነ ግብ ለማመቻቸት ሲባል የተመቻቸ የፈጠራ ታሪክ እንጂ የእውነት ጭላንጭልም እንደሌለበት ልቦናቸው ስለሚያውቀው፤ ይህንን የፈጠራ ወሬ የማባዛትና የማራባት አባዜ ስለ ተጠናውቷቸው እንጂ ምንም ዓይነት ማስረጃ እንደሌላቸው አስቀድመውም ስለሚያውቁት በቀጥታ እንዲህ አሉኝ ብለው ለመቅረብ አልቻሉም። በመሆኑም፤ ሐጎስ በየተኛውም መንገድ ሊያበጃጁት ቢሞክሩ የሌለውን ነገር እንዳለ አድርጎ ማቅረብ አይቻልምና አሜሪካም ሆነ ኤውሮጳ የሚኖሩ ዜጎች፤ የኢሮብ ወጣቶችን ወደ ኤርትራ እየመለመሉ ያስኮበልላሉ፤ በማለት ያቀረቡትን ክስ ተጨባጭ ማድረግ አልቻሉም፤ አይችሉምም። ስለሆነም፤ የሐጎስ ዮሐንስ ውንጀላ ከተራ የፈጠራ ቅጥፈት የዘለለ ሆኖ ሊወሰድ የሚችል አይደለም። አይደለም ማስረጃ አለኝ የሚሉ ከሆነ ደግሞ ሜዳውም ፈረሱም ይኸው አሁንም አለኝ የሚሉት ማስረጃም ሆነ መረጃ ካለ ለህዝብ ይፋ እንዲያደርጉ እንደሚጠበቅባቸው ልብ ሊሉት ይገባል።

(ፓራግራፍ 6 13ኛ መስመርን ይመልከቱ)

> ***"ከናንተ በውጭ አገር ከምትኖሩ ወገኖቻችን የተደበቀ ምንም ሚስጢር አለ ብለን አናምንም።.... ሁሌ የታመነና የተዋጣለት እውነተኛ ዜና ከናንተ በባሕር ማዶ ከምትኖሩ ወገኖቻችን ለማግኘት እንጠብቃለን።...."***

ከዚህ አባባል ውስጥ "በውጭ አገር ከምትኖሩ ወገኖቻችን የተደበቀ ምንም ሚስጢር አለ ብለን አናምንም" የሚለው የሌለ ፍጹማዊነትን ገላጭ መስሎ የሚታይና ከእውነት የራቀ መሆኑን ተግባብተን የምናልፈው ጉዳይ ይሆናል። ሆኖም፣ ሐጎስ ዮሐንስ ከተነገሩኝ ውስጥ አንዳንድ ነገሮችን መጥቀስ እወዳለሁ በማለት ከላይ ተተርጉሞ የቀረበውን በጥቅስ ምልክት ውስጥ አስገብተው ያስቀመጡት እውነት ይሆን? የሚል ጥያቄ በአንዳንድ የዋሆች አእምሮ ውስጥ ሊነሳ ይችል ይሆናል። ሆኖም፣ ያቀረቡት ፅሑፍ ከመጀመርያ እስከ መጨረሻ የተፋለሰና ቅንነት የጎደለው መሆኑን ለታዘበ ይህ ከላይ ያስቀመጡትና ተነገረኝ ያሉት ጉዳይ እውነት ባይሆን ብዙም የሚያስገርም ሆኖ እንደማያገኘው የሚያጠራጥር አይሆንም። ሐጎስ ዮሐንስ ተነገረኝ የሚሉትን ዓይነት አገላለጽ የተጠቀሙ አንዳንድ የዋህ ወገኖቻችን እንኳ ቢኖሩ፣ አባባሉ የአጠቃላዩን ሕብረተ-ሰባችን አመለካከት የማያንጸባርቅና የማይወክል በመሆኑ፣ በሳል ቢሆኑ ኖሮ አባባሉን ሊዘሉት በቻሉ ነበር።

እውቀት የሚባል ነገር እጅግ ዘርፈ ብዙ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ስለሆነም፣ ወላጆቻችን የሮኬት ጠበብት ባይሆኑም አከባቢያቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ ሕብረተ-ሰባቸው ውስጥ ለሚካሄደው ነገር ከአሜሪካም ሆነ ከኤውሮጳ መረጃና ማጣቀሻ የማያስፈልጋቸው፣ በራሳቸው መንገድ ነገሮችን አብጠርጥረውና አብጠልጥለው የሚተነትኑና የሚወግኑ ታላለቅ ሰዎች እንደሆኑ ለሰኮንድም ቢሆን ጥያቄ ውስጥ መግባት የሌለበት ጉዳይ ነው። በመሆኑም፣ በተለያየ ምክንያት ከኢሮብ ወደ ኤርትራ የሚኮበልሉ ወጣቶቻችን የፍልሰት ምክንያትና ሂደት እንዲነግሯቸው ኤውሮጳና አሜሪካ ተሰደው የሚኖሩትን "ሊቃውንቶች" ይጠይቃሉ ብሎ ለማሰብም ሆነ ለማመን ይከብዳል። ስለሆነም፣ *"ሁሌ የታመነና የተዋጣለት እውነተኛ ዜና ከናንተ በባሕር ማዶ ከምትኖሩ ወገኖቻችን ለማግኘት እንጠብቃለን።"* ብለውኛል የሚለው አገላለጽ ሚዛን የሚደፋ ሆኖ አይገኝም። ለዚህም ሐጎስ ዮሐንስ ራሳቸው ያቀረቡት ፅሑፍ በራሱ እንደ ማስረጃ ሊጠቀስ የሚችል ነው። ምክንያቱም፣ ሐጎስ ዮሐንስ ራሳቸው ከባሕር ማዶ ከምንኖር ወገኖች አንዱ ቢሆኑም፣ በፅሑፋቸው ውስጥ ካስነበቡን አንጻር ሲመዘን በጉልበት ልያግቱን ያሰቡት የፈጠራ ዝባዝንኬ "ከባሕር ማዶ ከሚኖሩ ወገኖች የሚገኘው ዜና ሁሌ የታመነና የተዋጣለት እውነትኛ" ሊሆን አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን ሃቁ በተቃራኒውን ሆኖ በመገኘቱ ነው። ከዚህም ሌላ አባባሉ እውነት የማይሆንባቸው ቢያንስ ሁለት ምክንያቶችን እዚህ መጥቀስ ይቻላል፣

ሀ/ ሐጎስ ዮሐንስና ይህ ፀሐፊ በባሕር ማዶ ከሚኖሩት ጋር የሚቆጠሩ ሲሆን ቢያንስ ሐጎስ ዮሐንስ የተጠበቀውን (ከሆነ ማለት ነው) "የታመነና የተዋጣለት እውነተኛ ዜና" ለማቅረብ እንደማይችሉ በጽሑፋቸው የተጋለጠ በመሆኑ፣

ለ/ እነዚህ ዓይነት ወሬዎችን ለመቃረም ወደ ባሕር ማዶ አንጋድዶ የሚጠብቅ ደካማና ተስፋ አጥ የሆነ ህዝብ ስለሌለን፣

ውድ አንባቢ፣ ሐጎስ ዮሐንስ ተነገረኝ ሲሉ ያሰፈሩትን ተመልክተናል። ግን እስቲ መለስ ብለን እያንዳንዳችን በተለይ ከኢሮብ መሬት ውጭ የምንኖር ወገኖች ራሳችንን እንመርምር። በዚህ

በኩል ይህ ፀሐፊ የራሱን ልምድ ለማካፈል ዝግጁ ነው። የዚህ ፀሐፊ ልምድ ደግሞ ምናልባት የሁሉም ባይሆን የብዙዎቹ እንደሚሆን አያጠራጥርም። ከጊዜ ወደ ጊዜ ስለ ቤተ-ሰብ፤ ጓደኛ፤ ቤተ-ዘመድና አገር፤ ህዝብ፤ ዝናብ ለመጠየቅ አገር ቤት ከሚኖሩ ወገኖቹ ጋር እንደ ሁኔታው በተለያየ መልክ ይገናኛል። በዚህ መልክም መቃረም ያለበት ዜና ብጤ ቢኖር ከዛ ይቃርማል። በበኩሉ አስፈላጊ ሆኖ የሚያካፍለው ዜና ቢኖር እዚሁ በሚኖርበት አገር የተከሰቱና የታዩ ክንዋኔዎች ላይ ያተኮሩ ብቻ ናቸው። ከዛ አልፎ በሚኖሩበት፤ ውለው በሚያድሩበት ቦታ ውስጥ ስለሚከናወነው ነገር "የታመነና የተዋጣለት እውነተኛ ዜና" ሊያቀርብላቸው ፈጽሞ አይዳዳውም። አደርገዋለሁ ብሎ ቢሞክር ደግሞ ነገሩ "ቀባሪን አረዱት" እንደሚሆን ጠንቅቆ ያውቋል። ስለሆነም፤ አገር ቤት ለታዩ ክስተቶች በባሕር ማዶ ከሚኖረው ወገን "የታመነና የተዋጣለት እውነተኛ ዜና" ይገኛል ተብሎ እደሚታመን ለመስማት ለዚህ ፀሐፊ ይህ የመጀመርያው ከመሆኑም በላይ እንዲህ ዓይነት ራስን አግዝፎ ለማቅረብ የሚደረግ ሙከራ እንደማቅለሽለሽ እንደሚያደርገው ሳይገልጽ ለማለፍ አይፈልግም። ሆኖም ለዚህ **'ግኝታቸው'** "ሐጎስ ዮሐንስን እንኳን ደስ አለዎት" ሳይል ማለፍ አይሻም!!!!። አንድ ወይም ሁለት የዋሆች እንደዚህ ዓይነት አመለካከት ካንጸባረቁም አመለካከቱ ስሕተት መሆኑን ማስረዳት እንጂ ይህንን ይዞ ገበያ መውጣት በዚህ ፀሐፊ እይታ አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ ሐጎስ ዮሐንስ ሕብረተ-ሰቡን የሚያዩበት መነጽር ምን ያህል የተንሸዋረረ እንደሆነ ለመገመት ያስችላል። ከሁሉም የባሰው ግን ሐጎስ ዮሐንስ ራሳቸው የዛ የሚያወሩለት "የታመነና የተዋጣለት እውነተኛ ዜና" አቅራቢ ለመሆን አለመቻላቸው ነው። "ደግነት ከቤት ይጀምራል" ይባላልና ሐጎስ ዮሐንስ "የታመነና የተዋጣለት እውነተኛ ዜና" ማቅረብን በሚመለከት ራሳቸው ላይ እንዲዘምቱ ቢመከሩ መልካም ይሆናል።

(ፓራግራፍ 7 ላይ ይመልከቱ)

*"ከዚህም አልፎ ባይገርማቹህ አሁን ለጊዜው ሆን ብየ ሳላጋልጥ የተውኩዋቸው <u>በጽሑፍ የተቀመጡ ጭብጦች</u> (<u>DOCUMENTED FACTS</u>) አለ።"*

እኝህ ሰው አስገራሚም፤ አስቅኝም ናቸው! የኢሮብ ወጣቶችን ወደ ሻዓቢያ እያስኮበለለ የእሳት ራት ከማድረግ አልፎ የራሱን ወገን እንዲገድል በማድረግ ላይ ስለሚገኝ/ኙ ሰው/ዎች "በጽሑፍ የተቀመጡ ጭብጦች አሉኝ"፤ ግን ሆን ብዬ ለጊዜው ከማጋለጥ ተቆጥቤ አለሁ ይላሉ። እውነቱን ለመናገር ሐጎስ ዮሐንስ በፅሑፋቸው ውስጥ በተለያየ አገላለጽና ቅላጼ ራሳቸው ለራሳቸው የሰጡትን "ጀግንነት" አያሳይም ብቻ ሳይሆን ምልክቱም አይታይም። "በፅሑፍ የተቀመጡ ማስረጃዎችን" በእጁ ውስጥ አስገብቶ የኢሮብ ወጣቶችን ለሻዓቢያ የእሳት-ራት ለማድረግ የሚያስኮበልሉ ወንጀለኞች በዚህ እኩይ ተግባራቸው እንዲቀጥሉ መተው ጀግንነትን አያመላክትም። ጀግንነት እነዚህን ወንጀለኞች በእጅ የጨበጡትን ማስረጃ በመጠቀም በያሉበት ለፍርድ እንዲቀርቡ በማድረግ የሚገለጽ እንጂ በውሽልሽል የቃላት ጋጋታ አይደለም። ካልሆነ ጀግና የሚለው ቃል ለዚህ ፀሐፊና ለሐጎስ ዮሐንሰ ያለው ትረጓሜ ፍጹም ለየቅል ነው። በዚህ ፀሐፊ እምነት ጀግንነት ለስላሳ ብልትን (soft target) በመምረጥ የባለ ሥልጣንን ዓይን እያዩ ለማስደሰት የሚደረግ ሙከራን አያጠቃልልም። ይህ ዓይን ካወጣ አጎብዳጅነት፤ ከመጠን ካለፈ አድርባይነትንና የራስን ስብእና እንደመሸጥ የሚቆጠር ተግባር እንጂ የጀግንነት መገለጫ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል አይደለም። ከአንድ መልካም ኅሊና ካለው ዜጋ የሚጠበቅ ቁምነገር ቢኖር፤ በእጅ ገባ የሚባለውን ማስረጃ ለሕዝብ ይፋ በማድረግ፤ ሕብረተ-ሰቡ አለ የተባለውን ከላይ የተጠቀሰው ዓይነት ወንጀል ለማስቆም ኃይሉን አስተባብሮ እንዲሠራ አስፈላጊውን እንቅስቃሴ ማድረግ ይሆናል። ይህንን ለማድረግ የሚከፈለው መስዋእትነት ወንጀሉን በማስቆም የሕብረተ-ሰቡን የተረጋጋ ኑሮ ከማረጋገጥ

አንጻር ሲመዘን የተከበረና ሊበረታታ የሚገባው ጀግንነት ነው። ከሕብረተ-ሰቡም አክብሮትና ተአማኒነትን የሚያጎናጽፍ ከመሆኑም በላይ ከሚያጎበድዱለት መንግሥትም ይህንን ዓይነት ማስረጃ ቢያስረክቡ የበለጠ ውዳሴ ሊያስገኝላቸው ይችል እንደነበረ የሚያጠራጥር አይደለም።

ከዚህ አልፎ የሌለውን ነገር በመቀባጠር የተላኩበትን የሰዎችን መልካም ስም የማጉደፍ ተልእኮ ከማሳካት አንጻር ሲመዘን ላኪው ምን ውለታ እንደሚከፍላቸው ባይታወቅም ሌላ የሚፈይደው ነገር ካለመኖሩም በተጨማሪ ለህዝብ ትእዝብት ያጋልጣል። ስለሆነም፣ እውነት ላይ ያልተመሠረተ ነገር ከሳምንት ወሬ አያልፍምና የሐጎስ ዮሐንስም ሆኑ መሰሎቻቸው የፈጠራ ወሬም ለአንድ ሳምንት ያህል የአይዞህ ባይ ወዶ-ገብ ካድሬዎችን የውሸት ደስታ ከማጎናጸፍ ያለፈ ሊሆን አልቻለም። ለማነኛውም፣ ሐጎስ ዮሐንስ እንዲገነዘቡት የሚፈለገው እውነት ቢኖር "ተጨባጭ የፅሑፍ ማስረጃ" አለኝ እያሉ፣ ማስረጃውን ለህዝብ ይፋ ባለማድረግ ወንጀለኞቹ የወንጀል ተግባራቸውን እንዲቀጥሉ እንደማበረታታት የሚቆጠር መሆኑን ነው። በመሆኑም፣ ሐጎስ ዮሐንስ አለኝ የሚሉትን ማስረጃ ይፋ በማድረግ መወጣት የሚጠበቅባቸውን የሞራል ግዴታ መወጣት ነበረባቸው፣ የጽሑፍ ማስረጃው "ካላቸው" አሁንም ማውጣት አለባቸው ፣ ከአንድ ጀግና የሚጠበቀው አገርና ትውልድን ከጥፋት የማዳን ማኅበራዊ ግዴታቸውን እንደተወጡ ሊቆጠርላቸው የሚችለውም ይህንን ሲያደርጉ ብቻ ነበር። ሆኖም ሐጎስ ዮሐንስ እስካሁን የሚጠበቅባቸውን ሓላፊነት ለመወጣት አልቻሉም። ለሌለ ነገር ማስረጃ ማቅረብ አይቻልምና ማስረጃን ማቅረብ አልቻሉም፣ አችሉምም። በተግባር ያልሆኑትን ሆኖ ለመታየትና ከዛ ሊገኝ የሚችል ምናኝ ውለታ ቢኖር ለማትረፍ ሲሉ "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" እንዲሉ የሌለውን በጭንቅላታቸው ውስጥ እንዳለ አድርገው በመፍጠር በባዶ እጅ ራሳቸውን አግዝፈው ለማቅረብ የሞከሩ ቢሆንም፣ በዚህ ይዘውት በቀረቡት የፈጠራ ወሬ ዙርያ  የሞከሩት ሸር በአስከፊ መልኩ እንደከሸፈባቸው ዛሬ ሳይረዱት አልቀሩም። ከመምሰል ይልቅ ሆኖ ማሳየት የሚጠይቅ ዘመን ነውና ሐጎስ ዮሐንስ ጀግና ከመምሰል ጀግና ሆነው በመውጣት ተሳስቻለሁ ብለው ይቅርታ ቢጠይቁ ይበልጥ የሚያስከብራቸው ይሆናል። ካልሆነ ግን የጊዜ ጉዳይ እንጂ በሕግም፣ በታሪክም ሆነ በሞራል እንደሚያስጠይቃቸው ሊገነዘቡት ይገባል። ከዚህም ሌላ፣ ሐጎስ ዮሐንስ ለተወሰነ ጊዜዊ ጥቅም ሲሉ ያቀረቡትን ከእውነት ጋር ግንኙነት የሌለው ዝባዝንኬ ትረካ በሰላምና በመግባባት አብሮ ይኖር የነበረውና በጋራ ግብ የተሳሰረውን ህዝብ በማቃረን ወይም አንዱ በሌላው ላይ ጥርጣሬ እንዲያሳድር በማድረግ አሉታዊ ሚና በመጫወት ላይ እንደሚገኙ ሰላም ወዳድ ወገን በቅጡና በጊዜ ሊረዳው ይገባል።

(ፓራግራፍ 7ን ይመልከቱ)

> ***"እንደሚባለው/እንደሚሉት፣ ይህ ወደ ኤርትራ ተልከው የተመለሱ ወጣት ሴቶችና ወንዶች በቃላቸው ያረጋገጡት ቃል ነው። ወጣቶቹ ለተልእኮ ወደ አስመራ ሂደው፣ ተልእኮአቸውን ፈጽመው መመለሳቸውን አረጋግጧል።" ይህን እንዳለ በእንግልዝኛው ቢቀመጥ አሻሚነቱን ያስወግዳል። "The young girls and boys have claimed to have been sent to Asmara to Acomplish a mission and return to Ethiopia after achieving the goal."***

እውነቱን ለመናገር በዚህ አገላለጽ ውስጥ ግልጽ ያልሆነ፣ ግልጽ ሊደረግም ያልተፈለገ ሚስጢር መሳይ ነገር እንዳለበት ሆኖ የቀረበ ነው የሚመስለው። በርግጥ ደፈር ብለው በዚህ ዕለት፣ በዚህ ቦታ፣ በነእገሌ እንዲህ ዓይነት ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት ባይችሉም፣ አንድ ነገር እንዳለ አስመስለው ሊያጃጅሉን እየሞከሩ እንደሆነ ግን ለመገመት የሚከብድ አይደለም። የሆኑ ወጣቶች የሆነ ምንነቱ ያልታወቀ ተልእኮ ለማስፈጸም ወደ አስመራ መላካቸውና፣ ተልእኮአቸውንም በሚገባ

*ፈጽመው መመለሳቸውን በቃላቸው እንዳረጋገጡ በማስመሰል የሆነ የተጠቀለለ ምንነቱ ያልታወቀ ነገር እንዳለ ያበስሩናል። ይህንን የሚያረጋግጥ፣ ሊያቀርቡት ባይችሉም በጽሑፍ የተቀመጠ ማስረጃ እንዳላቸውም ይገልጻሉ። ትልቁ ቁምነገር ደግሞ ይህ ምንነቱ ያልተገለጸ በእጃቸው ማስጃራው የገባ ጭራቅ ነገር ከነዚህ የኢሮብ ወጣቶችን ወደ ሻዓቢያ ከሚያስኮበልሉ ወንጀለኞች ጉዳይ ጋር ተያይዞ መቅረቡ ነው። በእውነት እንነጋገር ከተባለ ሐጎስ ዮሐንስ ግራ ተጋብተው ግራ እያጋቡን መሆኑ ግልጽ ነው። ከላይ ሲተርኩልን የመጡት ለዓቅመ-አዳም ያልደረሱ የኢሮብ ወጣቶችን ወደ ሻዓቢያ በማስኮብለል ኢትዮጵያዊ ወገናቸውን በመውጋት ለሻዓቢያ ጭዳ የሚያደርጉ የኢሮብ ተወላጆች ስለመኖራቸው ነበር። አሁን የሚተርኩልን ታሪክ ደግሞ ከዛ ለየት ያለና የኢሮብ ወጣቶች ለተልእኮ ከኢትዮጵያ ወደ አስመራ መላካቸውና፣ ተልእኮአቸውንም በሚገባ ተወጥተው መመለሳቸውን የሚያስረዳ ሆኖ ይገኛል። እዚህ ላይ አንድ የተምታታባቸው ጉዳይ እንዳለ ይታያል። ካልሆነም፣ ማብራርያ ያስፈልጓል።*

*ሐጎስ ዮሐንስ በዚህ ፓራግራፍ ውስጥ የሚያወሩት ለዚህ ፀሐፊ እንደሚገባው! የሆነ ኃይል ከኢሮብ ወጣቶችን እየመለመለ አስመራ ውስጥ ተልእኮ ፈጽመው እንዲመለሱ እንደሚያደርግ ነው። እውነቱን ለመናገር አስመራ ውስጥ የሚፈጸም ሻዓቢያን የሚያስደስት ጥቃት ይኖራል ብሎ ለማመን የሚቻል አይደለም። ሻዓቢያም ቢሆን ደግና ህዝብን የሚያፋቅር ነገር መሥራትን ነው የማይችለው እንጂ ተራ የወሮበላ ተግባርን ለመፈጸም የሚያንስ ኃይል አይደለም። በመሆኑም፣ ሐጎስ ዮሐንስ እንደሚሉት የኢሮብ ወጣቶችን አስኮብልሎ ለሻዓቢያ ጭዳ ለማድረግ የሚሠራ <u>‘ቡድን</u>’ በርግጥ አስመራ ውስጥ በራሱ በሻዓቢያ ቁጥጥር ሥር የሚገኘውን በማስወገድ እንዲረዳው ለማድረግ አይሆንም። ሻዓቢያ በራሱ ቁጥጥር ሥር የሚገኘውን ለማስወገድ እንደማያንስ በተግባር የታየ ጉዳይ ነውና፣ ሊያስፈልገው የሚችልና እየሰራበትም ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ ችግር ሊፈጥርለት የሚችል ኃይልን ለማንቀሳቀስ ነው። ከዚህ አንጻር ሲታይ ሐጎስ የሚያወሩን በተቃራኒው ይመስላል። ሆኖም ግን ተምታትቶባቸዋል። ባንድ በኩል፣ ለሻዓቢያ ጭዳ ሆኖ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን እንዲወጋ ወጣቶቻችንን እየመለመሉ ወደ ኤርትራ የሚያስኮበልሉ የኢሮብ ተወላጆች መኖራቸውን በማስረጃ አረጋግጫለሁ ይሉናል። አለኝ የሚሉትን <u>‘ማስረጃ’</u> ለማቅረብ ግን አይችሉም፣ በሌለ ነገር ላይ ማስረጃ ማቅረብ ስለማይቻል ለወደፊትም እንደማይችሉ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። የሆነ ሆኖ በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ሐጎስ ዮሐንስ ያቀረቧቸው ሁለቱም ሁኔታዎች በአንድ ጊዜ ሊከሰቱ እንደሚችሉ ለመገንዘብ የማያስቸግር ቢሆንም፣ አሁን ያስቀመጡት ትንተናን መሠረት በማድረግ ሲታይ ግን የሚጣጣም ሆኖ አይገኝም። ስለዚህ ሐጎስ ሁለቱን ክስተቶች ማጣጣም ይጠበቅባቸው ነበር። ብቻ ምን ይደረግ! “ከቅዠት” የሚፈልቅ እውነት የለምና ሊያጣጥሙት ምን ጊዜም አይችሉም። ለማንኛውም፣ ራሳቸውም ሆኑ አይዞህ ባይ ወዶ-ገብ ካድሬዎች ይህንን ማብራራት ይጠበቅባቸዋል። ይህ ፀሐፊ እንደሚረዳው ከሆነ ግን፣ አንድ የሆነ ቡድን ከኢትዮጵያ ወደ አስመራ ተልኮ በስም ያልተጠቀሰ ጥቃት ፈጽሞ እንዲመለስ መልምሎ መሸኘቱን ነው። በጽሑፍ የተደገፈ መረጃ አለኝ የሚሉትም ከነዚህ አስመራ ውስጥ ጥቃት ፈጽመው እንደተመለሱ ከተናገሩት ወጣቶች በተገኘ ማስረጃ ላይ በመመርኰዝ መሆኑን የሀጎስ ዮሐንስ ፅሑፍ ይገልጻል። ምን ነው ነገሩ ተምታታሳ? ባንድ በኰል የኢሮብ ተወላጆች ለሻዓቢያ ጭዳ ሊሆኑ የሚችሉ ነብስ ያልገዙ የኢሮብ ወጣቶችን ወደ ኤርትራ ያስኮበልላሉ የሚል ውንጀላ ያቀርባሉ። በሌላ በኰል ደግሞ ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ ለግዳጅ የተላኩ የኢሮብ ወጣቶች አስመራ ውስጥ የተሰጣቸውን ተልእኮ ፈጽመው መመለሳቸውን የሚያረጋግጥ ከራሳቸው ከወጣቶቹ አንደበት የወጣ የፅሑፍ ማስረጃ በእጄ ይገኛል ይሉናል።*

ባጭር አነጋገር እዚህ ላይ ሐጎስ ዮሐንስ ምን ለማለት እንደፈለጉ ለዚህ ፀሐፊ ግልጽ ሊሆንለት አልቻለም። የጠቀሷቸው ወጣቶች አስመራ ሂደው የፈፀሙት ተልእኮ ምን እንደሆነ ምንም ፍንጭ አልሰጡም። አሳክተውት ተመለስን ያሉት ተልእኮ ምን እንደነበረ? የላካቸው ሰው ወይም ቡድንስ ማን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች መመለስ ነበረባቸው። ግን አልመለሱትም። ለምን ? ሐጎስ ዮሐንስ ስንክሳሩን ይፍቱት!!!

(ፓራግራፍ 7ን ይመልከቱ)

> *“ሌላው ያልተረጋገጠ ውንጀላ አንዳንድ በአሜሪካ ነዋሪ የሆኑ የኢሮብ ተወላጆች በሳውዲ ዓረብያና አስመራ ባላቸው የቤተሰብ ትስስር አማካኝነት የዚህ ተልእኮ ዋና ተዋኒያን መሆናቸው ይነገራል።”*

ሐጎስ ዮሐንስ ያልተረጋገጠ ወሬ “እንደሚያረጋግጠው” እያሉ የሚዘባርቁት ነገር ተደጋጋሚ አሰልቺም ነው። በጽሑፋቸው ውስጥ (allegation, alleged) የሚሉ ቃላቶች በብዙ ቦታዎች ተደጋግመው ይታያሉ። ሆኖም፤ ይህ ቃል የክስተቶችን ተጨባጭነት አያመላክትም። የሚገልጸው ጥርጣሬን ብቻ ነው። በሚናፈስ አሉባልታ ላይ በመመርኮዝ ይህን ዓይነት ውንጀላ ማስፈር ደግሞ ለግለሰቡም ሆነ ባጠቃላይ ለማኅበረ-ሰቡ ጤነኛ ግንኙነትና አብሮ መኖር እጅግ ጎጂ ነው። ማረጋገጫውና ማስረጃው ባይቀርብም እነዚህ አሜሪካና ሳውዲ ዓረብያ አሉ የሚባሉ ቤተሰቦች ፈጽሞዋቸዋል የሚሉት ወንጀል ምንነት ነጥሮ፣ በስሙ ተጠቅሶ ባይሰፍርም እንኳ፤ ከአቀማመጡ አንድ የሆነ ከበድ ያለ ወንጀል መፈጸሙን ያመላክታል። ይህን በሚመለከት ይህ ፀሐፊ ማስረጃውና ተፈጸመ የሚባለው ወንጀል ነጥሮና ተሰይሞ ሲወጣ እንደሁኔታው የሚደግፈው ወይም የሚቃወመው ጉዳይ ሊሆን ይችላል። እዚህ ላይ በዋናነት የሚነሳው ጉዳይ ግን እነዚህ ሐጎስ ዮሐንስ የሚያሙዋቸው “ቤተ-ሰቦች” ፈጸሙት የሚሉን ወንጀልና የኢሮብ ወጣቶችን ወደ ሻዓቢያ አስኮበለሉ በማለት የሚያቀርቡት ውንጀላ ሊጣጣም አለመቻሉ ላይ ነው። ሐጎስ ዮሐንስ እነዚህ ሁለቱን ተግባራት የሚፈጽመው ቡድን አንድ ነው የሚሉን ከሆነ በነዚህ ሁለት ክንዋኔዎች መካከል የሚታየውን ተቃርኖ አስታርቀው ያሳዩን። እነዚህ ሁለት ተግባራት የሚከናወኑት በሁለት የተለያዩ ቡድኖቻ ናቸው የሚሉ ከሆነ ደግሞ መጣጥፋቸውን መልሰው ይመርምሩ።

ለነገሩ ግን ዛሬ አነሰም በዛ ዕድሜ “ለፀሐዩ የኢህአዴግ መንግሥት” ዘመድ ወደ ሳውዲ ያልተሰደደበት አለ እንዴ? እና ሳውዲ ዓረብያና አስመራ ዘመድ ያላቸው ወገኖች በሙሉ ተጠርጣሪ ማድረግ ይቻላል? ተገቢስ ይሆናል? የሆነ ሆኖ ባለቤቱ ይጨነቁበት፤ የማታ ማታ “እሾ ላጣሪው” ይባላልና ራሱ ባጠረው እሾኽ የሚወጋ እንደሚኖር አያጠራጥርም።

(ፓራግራፍ 7ን ይመልከቱ)

> *“ለኔ ይህ ሁሉ ቅዠት ነበር። አሁንም ቅዠት ነው። አንድ የኢሮብ ተወላጅ ለዓቅመ አዳም ያልደረሱ የኢሮብ ወጣቶችን አደራጅቶ አሳዳጃቸው ጎን አስታጥቆ በማሰለፍ የኢሮቦችንና ኢትዮጵያዊያን ወገኖቹን ለማስገደል የሚሰራ አንድም እንኳ የኢሮብ ተወላጅ ይኖራል ብዬ አልገመትኩም። በዛን ጊዜም አላመንኩም፤ አሁንም ፈጽሞ አላምንም። ይህ ማለት ግን በጽሑፍ የተያዘ እውነተኛ ማስረጃ፤ እውነት አይደለም ማለቴ አይደለም።”*

የተለመደውና ቅጥ አምባሩ የጠፋበት የተምታታ እጅጉን በራስ መተማመን የጎደለበት የሐጎስ ዮሐንስ ቅዠት እዚህ ውስጥም ተደናብሮ ቀርቧል። ለነገሩ እዚህ ላይ የሚሉን በመሠረተ-ሓሳብ

ደረጃ ሲታይ ከላይ ደጋግመው እስኪሰለች ድረስ ካሉት የተለየ ያስቀመጡት ነገር የለም። ደጋግመው ያሉንና አሁንም የሚሉን ያው የተለመደው "ያኔም አላመንኩም፤ አሁንም ፈጽሞ አላምንም" ነው። ሆኖም "በጽሑፍ የተያዘ እውነተኛ ማስረጃ፤ እውነት አይደለም ማለቴ አይደለም" በማለት ያክሉበታል። ሐጎስ አንድ እውነት ብቻ ነው በአንድ ጉዳይ ላይ ሊኖር የሚችለው። ይኸውም፤ ወይም ያኔም አላመኑም፤ አሁንም አያምኑም፤ ካልሆነ ደግሞ በጽሑፍ የተያዘ እውነተኛ መረጃ አለዎት አውጥተው ለህዝብ ይፋ ያርጉት። ካልሆነ በአንድ በኩል እኔ አላምንም እያሉ በሌላ በኩል በጽሑፍ የተያዘ እውነተኛ ማስረጃ አለ፤ የሚል ክርክር ትርጉም የሚሰጥ አይደለም። በጽሑፍ የተያዘ እውነተኛ ማስረጃ አለኝ ካሉ "አላመንኩም አላምንም" የሚሉ ቃላቶች ለትእዝብት የሚተርፉ እንጂ ከማዳመቅያነት የዘለለ ትርጉም ሊኖራቸው ፈጽሞ አይቻልም። እርስዎም በጽሑፍ የሰፈረ "በእጅዎ" የሚገኝ "እውነተኛ ማስረጃን" የመቀበልና የማመን ሓላፊነት እንዳለብዎት ሊዘነጉት የማይገባ ሃቅ ነው። ስለሆነም፤ ማስረጃውን ለህዝብ ይፋ የማድረግ ሐላፊነትም ግዴታም እንዳለብዎት ሊዘነጉት የማይገባ የህዝብና የአገር ታላቅ ጉዳይ ነው። ለነገሩ በዚህ የሰው ንግድ እንበለው ኩብለላ አንድም የኢሮብ ተወላጅ ይኖራል ብለው ካልገመቱ፤ ያኔም ካላመኑና አሁንም ፈጽመው የማያምኑት ከሆነ፤ ይህንን ዓይነት አስነዋሪ ጽሑፍ ለማውጣት ያነሳሳዎት ምክንያት ምን ይሆን? ፈር የለቀቀ የሆነ ዓይነት የሚታይ ወይም የማይታይ ጥቅም ለማግኘት ሰብአዊ ኅሊናን በመሸጥ? ወይስ የሆነ ለሕይወት የሚያሰጋ የተጫነብዎት ማስፈራርያ ስላለ? ወይስ ሌላ እኛ አንባቢዎች ያለተገነዘብነው ጉዳይ ስላለ? መልሱን የምናገኘው ከሐጎስ ዮሐንስ ብቻ ነው። ለዓቅመ አዳም የደረሰ ሰው መቸም አንድ ነገር ተራ ቅዠት መሆኑን እያወቀ የሆነ ጥቅም አገኝበታለሁ ብሎ ካላሰበ እንዲሁ ለክፋት ወይም ለተራ ዝና ብሎ እንዲህ ዓይነት አስነዋሪ ጽሑፍ ያወጣል ተብሎ የሚጠበቅ ፈጽሞ አይሆንም። ስለሆነም፤ ሐጎስ ዮሐንስ አሁንም ቢሆን ይህ ጉዳይ በታሪክም፤ በሕግም ሆነ በሞራል የሚያስጠይቅ መሆኑን ተገንዝበው **'በእጃቸው የሚገኘውን እውነተኛ የጽሑፍ ማስረጃ'** ጀባ ሊሉን እንደሚገባ ሳያስገነዝቡ ማለፍ አገባብ አይደለም ብሎ ይህ ፀሐፊ እንደሚያምን ሊያሰምርበት ይወዳል።

ይቀጥላል................!!

ጥቅምት 3 ቀን 2011 ዓ.ም.ፈ

ለአስተያየት balibizema@yahoo.com ይጠቀሙ!